## የእድገት ቁጥጥር፣ ማጣራት፣ እና ግምገማ:

# በ ዲሲ ለሚገኙ የጤና እና የቀደመ ትምህርት አቅራቢዎች መመሪያ

DC AUTISM COLLABORATIVE

## የእድገት ቁጥጥር/ክትትል

| | የጤና አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | የቀደመ እንክብካቤ እና ትምህርት አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | ከቤተሰቦች ጋር እንዴት አጋርነት መፍጠር ይቻላል |
|---|---|---|---|
| የእድገት ቁጥጥር ወይም ክትትል ማለት ንቁ የሆነ አሁን-ላይ እየሰራ ያለ ልጆች ሲያድጉ የሚመለከት እና ስለ ልጆች ክህሎቶች እና አቅሞች በቀላጆች እና አቅራቢዎች መካከል ዉይይቶች እንዲኖሩ የሚያበረታታ ሂደት ነዉ።<br><br>የእድገት ቁጥጥር የእድገት ክትትልን ይደግፋል እና ያሟላል(ነገር ግን አይተካዉም)። | የአሜሪካ አካዳሚ ኦፍ ፔዲያትሪክስ (ኤኤፒ) በሁሉም ደህና-ልጅ ጉብኝቶች ላይ የእድገት ክትትል ይመክራል። ይህም የሚያካትተዉ:<br>• የእድገት ታሪክን ይገመግማል፣<br>• ስለ ስጋቶች ይጠይቃል፣<br>• ጥንካሬዎች እና ስጋቶችን ይገመግማል፣<br>• ልጁን ይከታተላል፣<br>• መዝገብ ይይዛል፣<br>• እና እርስ በእርስ ዉጤቶችን ያጋራል።<br><br>ወላጆች በጉብኝቶች መካከል የሚኖረዉን ወሳኝ ደረጃዎች እንዲቆጣጠሩ እና ዉጤቶችን ከፔዲያትሪሺያኖች እና ሌሎች አቅራቢዎች(ይህም ማለት የትምህርት አቅራቢዎች) ጋር እንዲያጋሩ ያበረታታል። | የቀደመ እንክብካቤ እና ትምህርት አቅራቢዎች ሊያደርጉ የሚችሉት:<br>• የልጁን እድገት ለመቆጣጠር በየጊዜዉ የወሳኝ ደረጃዎች ማረጋገጫ ዝርዝር ጥቅም ላይ ማዋል<br><br>ቤተሰቦች የልጃቸዉን እድገት በቤት ዉስጥ እንዲቆጣጠሩ እና ለአስተማሪዎች እና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ዉጤቶችን እንዲያጋሩ ማበረታታት | ወላጆች እዚህን እንዲያደርጉ ሊበረታቱ ይችላሉ:<br>• የልጃቸዉን የእድገት ወሳኝ ደረጃዎች በእነዚህ የጊዜ ቆይታዎች (2፣ ፣ 6፣ እና 9 ወራቶች፣ 1 ዓመት፣ 15 እና 18 ወራቶች፣ 2 ዓታቶች፣ 30 ወራቶች፣ 3፣ 4 እና 5 ዓመታቶች)ይህን በመጠቀም መከታተል **ነጻ ወሳኝ ደረጃዎች መከታተያ**<br>• ዉጤቶች እና ስጋቶችን ለጤና እና ትምህርት አቅራቢዎች ማጋራት |
| አቅሮቦቶች: | **ኤኤፒ የመከላከል ፔዲያትሪክ ጤና እንክብካቤ ምክሮች**<br>**የ ሴንተርስ ፎር ዲዚዝ ኮንትሮል ኤንድ ፕሪቨንሽ (ሲዲሲ) የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ፕራይመር**<br><br>**የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር ያለባቸዉን ልጆች መለየት እና መንከባከብ: ለፔዲያትሪክ ክሊኒኮች የሚሰጥ ኮርስ** | **የሲዲሲ የልጅ ማግኘት ፕራይመር**<br><br>**የሲዲሲ የቀደመ እንክብካቤ እና ትምህርት አቅራቢዎች ፕራይመር**<br><br>የሲዲሲ ነጻ 1-ሰዓት ኦንላይን ስልጠና።<br>**እኔን ይመልከቱኝ! ወሳኝ ደረጃዎችን ማክበር እና ስጋቶችን ማጋራት** | **የሲዲሲ "ምልክቶቹን ይማሩ። ቀድመዉ እርምጃ ይዉሰዱ" ፕሮግራም አቅርቦቶች**<br><br>**ቀደመዉ እርምጃ ይዉሰዱ** ዌብሳይት |

*ግንቦት 2022*

# የእድገት ማጣሪያ እና ጥቆማ

| | የጤና አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | የቀደመ እክብካቤ እና ትምህርት አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | ከቤተሰቦች ጋር እንዴት አጋርነት መፍጠር ይቻላል |
|---|---|---|---|
| የእድገት ማጣሪያ ልጆች እንዴት እያደጉ እንደሆነ በቅርበት ይመለከታል። ልጁ አጠር ያለ ምርመራ ይደረግለታል፣ ወይም ወላጆች ስለ ልጃቸዉ መጠይቆችን እዲሞሉ ይደረጋል።<br><br>ለማጣሪያ የብዙ-ደረጃ አካሄድ መከተል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ለአጠቃላይ የእድገት ስጋቶች የሚሆኑ የማጣሪያ መሰሪያዎች አንዳንድ ጊዜ ላይ **“ደረጃ 1 ማጣሪያ መሰሪያዎች”** ይባላሉ። ለተለየ የእድገት ስጋቶች የሚሆኑ የማጣሪያ መሰሪያዎች፣ ይህም የኦቲዝም ምልክቶችን ያካትታል፣አንዳንድ ጊዜ ላይ **“ደረጃ 2 ማጣሪያ መሰሪያዎች”** ይባላሉ። የደረጃ 1 ማጣሪያ መሰሪያ ችግሮችን መለየት ከቻለ፣ የደረጃ 2 ማጣሪያ መሰሪያ የሚመከር ይሆናል። የደረጃ 1 ወይም ደረጃ 2 ማጣሪያ መሰሪያ ችግሮችን መለየት ከቻለ፣ ልጁ ለቀጣይ ግምገማዎች ጥቆማ የሚደረግለት ይሆናል። | ኤኤፒ መስፈርት የወጣለት የእድገት ማጣሪያ በ 9፣ 18፣ እና 30 ወር ደህና-ልጅ ጉብኝቶች ላይ እንዲደረግ ይመክራል፣ መስፈርት የወጣለት ኦቲዝም ማጣሪያ በ 18 እና 24 ወር ደህና-ልጅ ጉብኝቶች ላይ እንዲደረግ ይመክራል። አሁን ላይ ለሚገኙ እና አዲስ መጪ ለኦቲዝም-የተለዩ ማጣሪያ መሰሪያዎች ሙሉ ዝርዝር፣ እባክዎትን ሰንጠረዥ 6 ይመልከቱ **2020 ኤኤፒ የኦቲዝም ክሊኒካል ሪፓርት**።<br><br>ስጋት ያለበት ዉጤት ያላቸዉ ልጆችን ለቀጣይ ግምገማ ይጠቁሙ።<br><br>የሕክምና አቅራቢዎች ለአይኤፍኤስፒ/አይኢፒ ብቁነት ግምገማ በተመሳሳይ ጊዜ ቤተሰቦችን ለጠንካራ አጀማመር ወይም ቀዳሚ ደረጃዎች መጠቆም አለባቸዉ።<br><br>• **ጠንካራ አጀማመር** (ከዉልደት እስከ 2 ዓመታቶች፣ 10 ወራቶች) ወይም<br>• **ቀደሚ ደረጃዎች** (2 ዓመታቶች፣ 8 ወራቶች እስከ 5 ዓታቶች፣ 10 ወራቶች) | አጠቃላይ የእድገት ማጣሪያ (መስፈርት የወጣለት የማጣሪያ መሰሪያን በመጠቀም) እድሜያቸዉ 0-5 ለሚሆኑ ልጆች ወደ ሄድ ስታርት እና አርሊ ለርኒንግ ኲዋሊቲ ኢምፐሩቭመንት (ኪዉአይኤን) በታዎች በሚገቡበት ወቅት በመጀመሪያዎቹ 45 ቀናቶች፣ እንዲሁም ከዚያ ቀጥሎ በየዓመቱ መሰጠት አለበት። በተጨማም፣ ዲሲፒኤስ የእድገት ማጣሪያ በአዲስ መልክ ወደ ፒኬ3 እና ፒኬ4 ለገቡ ተማሪዎች በመጀመሪያዎቹ 45 ቀናቶች እንዲሰጥ ይፈልጋል።<br><br>**ልጁ ይህ የሚታይበት ከሆነ**<br><br>• በማጣራት ሂደት ተገቢ በሆኑት የማጣሪያ መሰሪየዎች/ጎራዎች ፓዘቲቭ ከሆነ (ለምሳሌ፣ ኤም-ሲኤችኤቲ፣ የኤኤስኪዉ የግል-ማህበራዊ ጎራ) ወይም<br>• ኦቲዝም የሚጠቁም **ጠቋሚዎች ወይም ምልክቶች** የሚያሳይ ከሆነ ወይም<br>• ወላጆች ልጃቸዉ ኦቲዝም አለበት የሚል ስጋት ካለባቸዉ<br><br>**እንደዛ ከሆነ ልጁ ለእነዚህ በአንዱ ጥቆማ ሊደረግለት ይገባል**<br><br>• **ጠንካራ አጀማመር** (ከዉልደት እስከ 2 ዓታቶች፣ 10 ወራቶች) ወይም<br>• **ቀዳሚ ደረጃዎች** (2 ዓመታቶች፣ 8 ወራች እስከ 5 ዓመታቶች፣ 10 ወራቶች)<br><br>ጠንካራ አጀማመር/ቀዳሚ ደረጃዎች ቤተሰቦች ስጋቶቻቸዉን እና የማጣሪያ ዉጤቶችን ከሕክምና አቅራቢዎቻቸዉ ጋር ማጋራት እንዲችሉ ያበረታታቸዋል እና የማህበረሰብ አቅርቦቶችን ያጋሉ። | ወላጆች የኢስተር ሲልስ ኦንላይን**እድሜዎች እና ደረጃዎች መጠይቆችን** ማግኘት ይችላሉ። ቤተሰቦች የማጣሪያ ዉጤቶችን ለልጃቸዉ የጤና እና ትምህርት አቅራቢ ማጋራት አለባቸዉ።<br><br>የማጣሪያ መሰሪያዎች ዉጤቶች በ **ማጣሪያ ፓስፓርት** ሊመዘገቡ ይችላሉ።<br><br>በተጨማም፣ ቤተሰቦች በልጃቸዉ እድገት ላይ ስጋት ካደረባቸዉ፣ እነዚህን ማድረግ ይችላሉ:<br><br>• ሄልፕ ሚ ግሮዉ ዲሲ ጋር በስልክ ቁጥር 1-800-ማም-ቤቢ (1-800-666-2229) መደወል እና ከእንክብካቤ አስተባባሪ ጋር መነጋገር ይችላሉ። ኤችኤምጂ ዲሲ (እርጉዝ ለሆኑ እናቶች እና እድሜያቸዉ ከ 0-5 ዓመታቶች ለሆኑ በዲሲ ለሚኖሩ ልጆች) በማጣሪያ ሂደት(ኤኤስኪዉ እና ኤኤስኪዉ-ኤስኢ በመጠቀም) እና/ወይም በጥቆማዎች ሊደግፉ ይችላሉ።.<br>• የጠንካራ አጀማመር ልጅ ማግኘት የነጻ ስልክ መስመር ላይ በስልክ ቁጥር (202) 727-3665 መደወል ወይም ልጃቸዉ ከዉልደት እስከ 2 ዓመታቶች፣ 10ወራቶች ከሆነ **የጥቆማዎች ቅጽ** መሙላት ይችላሉ<br>• የቀደመ ደረጃዎች ጋር መደወል ወይም ልጃቸዉ ከዉልደት እስከ 2 ዓመታቶች፣ 8 ወራቶች እስከ 5 ዓመታቶች፣10ወራቶች ከሆነ **ቀዳሚ ደረጃዎች ጥቆማዎች ቅጽ መሙላት** ይችላሉ<br>• የተለየ ትምህርት ግምገማ ሂደትን ለመጀመር ፍቃድ ማቅረብ<br>• ከትምህርት ቤታቸዉ/የልጅ እንክብካቤ ወይም ሰራተኞች እና የዋና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር መነጋገር |
| አቅርቦቶች | የጤናምርመራ ስልጠና እና አቅርቦቶች ማዕከል**ለጎራ-የተለየ የማጣሪያ መሳያዎች** ገጽ 10 ይመልከቱ | **የጠንካራ አጀማመር ፓሊሲዎች**<br><br>የጠንካራ አጀማመር ነጻ ስልክ መስመር: 202-727-3665 ወይም ጥቆማዎችን ማድረግ **ኦንላይን ጥቆማ ቅጽ**<br><br>ቀዳሚ ደረጃዎች **የጥቆማ ቅጽ** | |

# ግምገማ

| | የጤና አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | የቀደመ እንክብካቤ እና ትምህርት አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | ከቤተሰቦች ጋር እንዴት አጋርነት መፍጠር ይቻላል |
|---|---|---|---|
| የእድገት ግምገማ የልጆች እድገት ላይ ጠለቅ ያለ ምልከታ ያደርጋል፣ አብዛኛዉን ጊዜ ላይ በሰለጠነ ስፔሻሊስት ይደረጋል(ለምሳሌ፣ የእድገት ፔዲያትሪሺያን፣ ሳይኮሎጂስት፣ የንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂስት)። ስፔሻሊስት ልጆችን የሚመለከት፣ቅርጽ ያለዉ ምርመራ የሚሰጥ፣ እንክብካቤ ሰጪዎችን ቃለ መጠይቅ የሚያደርግ፣ እና/ወይም እንክብካቤ ሰጪዎች መጠይቆችን እንዲሞሉ የሚጠይቅ ይሆናል። የዚህ መደበኛ ግምገማ ዉጤት ልጁ ለኤኤስዲ መስፈርቶች ማሟላቱን ለይቶ ያዉቃል እና ምክሮችን ይሰጣል (ምሳሌ፣ ልጁ መዉሰድ ያለባቸዉ የጣልቃገብነት አገልግሎቶች)። | ለኤኤስዲ **ዲኤስኤምS—5 ምርመራ መስፈርቶችን** ይጠቀማል።<br><br>ተቀባይነት ያለዉ የቋንቋ፣ ማገናዘብ፣ እና የመላመድ ብቃቶች እዲሁም የስሜት ህዋሳት ሁኔታ(መስማት፣ ማየት፣ እና የስሜት ህዋስ ማቀናበር) ግምገማ።<br><br>የግምገማዉ ወሳኝ አካላት:<br>• የወላጅ ሪፓርት<br>• ያልተዛባ ዉሂብ/ ግምገማ መሳሪየዎች (ምሳሌዎችን ይመልከቱ)<br>• ልጁን መመልከት<br>• የምርመራ ግብረ መልስ እና የሕክምና ምክሮች<br>• የተጻፈ ሪፓርት | ጠንካራ አጀማመር እና ቀዳሚ ደረጃዎች የሚመሩት በኢንዲቪጁዋልስ ዊዝ ዲስኤቢሊቲስ አክት **ክፍል ሐ** እና **ክፍል ለ** ነዉ።<br><br>ቀዳሚ ደረጃዎች እና ሁሉም የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ይህም የቻርተር ትምህርት ቤቶችን ያካትታል) ለኤኤስዲ ትርጉም **ኢንዲቪጁዋልስ ዊዝ ዲስኤቢሊቲስ ኤዱኬሽን አክት** ጥቅም ላይ ያዉላሉ።<br><br>ጠንካራ አጀማመር እና ቀዳሚ ደረጃዎች ግምገማዎች እነዚህን የእድገት አካባቢዎችን; አካላዊ፣ እይታ እና መስማት ያካትታል; ማገናዘብ; ማህበራዊ-ስሜታዊ; እና የመላመድ ክህሎቶችን ይመለከታሉ።<br><br>የጠንካራ አጀማመር ግምገማ<br>• ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ብቃታቸዉ በተረጋገጠ ስፔሻሊስቶች የያዘ ሁሉን አቀፍ በሆነ ቡድን(ኤምዲቲ) መካሄድ አለበት<br>• ኤምዲቲ የልጁን ታሪክ(ወላጆችን ቃለ መጠይቅ ማድረግን ያካትታል)፣እድገት፣ አሁን ላይ ያለዉ ጥንካሬዎች እና ተግዳሮቶች፣ እና የሕክምና፣ ትምህርት፣ እና ሌላ መዝገቦች የግምገማ መሳሪያ እና ፍተሻ/ግምገማ መቆጣጠር አለበት።<br><br>ቀዳሚ ደረጃዎች እነዚህን ያካትታል፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ:<br>• የወላጅ ሪፓርት<br>• የአስተማሪ ሪፓርት<br>• የመማሪያ ክፍል እ/ወይም ማዕከል-ላይ የተመሰረተ ምልከታዎች<br>• ልጁን መመልከት<br>• በወላጅ/አስተማሪ የተሞላ መጠይቆች<br>• በገምጋሚ-የተሞላ ጨዋታ-ላይ የተመሰረተ ወይም በከፊል-የተዋቀረ ምልከታዎች<br>• ፍቃድ የተሰጠዉ ተያያዥ አገልግሎቶች አቅራቢ ወይም የተለየ አስተማሪ የተሞላ ተገቢ የሆነ የግምገማ መሳሪያዎች ቁጥጥር። | በግምገማዉ ሂደት ወቅት፣ ወላጆች ይህን ያደርጋሉ:<br>• ከአቅራቢዉ ጋር ሁሉን ያካተተ ቃለ መጠይቅ ላይ ይሳተፋሉ<br>• መስፈርት ያላቸዉ መጠይቆችን ይሞላሉ<br><br>ወላጆች ከአቅራቢዎች እና ኤጀንሲዎች ጋር የተደረጉ የዉይይቶች እና ግንኙነቶች መዝገቦችን ማስቀመጥ አለባቸዉ። ሴንተር ፎር ፓረንትስ ኢንፎርሜሽን ኤንድ ሪሶርስስ ይህን አዘጋጅቷል **ናሙና መዝገብ-ማስቀመጫ ስራ ሉህ**። |
| አቅርቦቶች: | ለበለጠ ዝርዝር፣ እባክዎትን ሰንጠረዥ 6 ይመልከቱ **2020 ኤኤፒ ክሊኒካል ሪፓርት በ ኦቲዝም** እና **የኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደርስ መሳሪያዎች ስብብስ ለፔዲያትሪክ ዋና እክብካቤ አቅራቢዎች በኮሎምቢያ ዲስትሪክት** | ጠንካራ አጀማመር ዓመቱን-በሙሉ የሚሰጥ በፈቃደኝነት፣ ተለዋዋጭ፣ እና ነጻ አገልግሎቶች ያቀርባል።<br><br>ሁሉም የቀደመ ደረጃዎች አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ነጻ ናቸዉ። | **ቤተሰቦች መብቶች አሉዋቸዉ: አይዲኢኤ ክፍል ሐ የአካሄዶች መጠበቂያዎች**<br><br>**የኮሎምቢያ ዲስትሪክት አይዲኢኤ ክፍል ለ የአካሄዶች መጠበቂያዎች ማሳወቂያ እክሎች ላሉባቸዉ ተማሪዎች ወላጆች** |

# ከግምገማዎች በኋላ

| | የጤና አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | ቀዳሚ እንክብካቤ እና የትምህርት አቅራቢ ሚና እና ሃላፊነቶች | ከቤተሰቦች ጋር እንዴት አጋርነት መፍጠር ይቻላል |
|---|---|---|---|
| ከእድገት ግምገማዎች በኋላ የሚኖረዉ ወቅት አብዛኛዉን ጊዜ ላይ ለቤተሰቦች ተግዳሮት ያለበት ይሆናል፣ ምክንያቱም ለልጃቸዉ ጉዳይ ተቆጣጣሪ ሚናን የሚጫወቱበት ጊዜ ስለሚሆን ነዉ። እነርሱ ተገቢ አገልግሎቶችን እና ድጋፎችን ለልጃቸዉ ለማግኘት ዉስብስብ ስርዓቶችን እንዴት ማሰስ እንደሚችሉ መማር አለባቸዉ። በርካታ ቤተሰቦች ሪፓርት እንደሚያደርጉት ይህ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ አስጨናቂ እና ከአቅም በላይ ይሆናል እና ተመራጩ የሆነዉ ልምድ እንክብካቤ ይህን ቀጣይ ደረጃ እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ የሚያስረዳቸዉ ድጋፎችን እንዲያገኙ መርዳት ነዉ (ለምሳሌ፣ የወላጅ ድጋፍ ቡድኖች፣ እንክብካቤ ማስተባበሪያ፣ ለጉዳይ ቁጥጥር አገልግሎቶች የማህበራዊ ስራ)። | እነዚህ ግምገማዎች የኤኤስዲ ሕክምና ምርመራ ዉጤት ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህም ልጁ በይበልጥ ተለይተዉ የተዘጋጁ ከጤና-ጋር ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይፈቅድለታል፣ ይህም የሚያካትተዉ ተለይተዉ የተዘጋጁ ኢንሹራንስ**(የተለየ ፍላጎቶች ላሉዋቸዉ ልጆች የጤና አገልግሎቶች፣ኢንክ.)** እና ጣልቃ ገብነቶች (ለምሳሌ፣ ተግባራዊ የሚሆን የባህሪ ትንታኔ)።<br>ቤተሰቡ የኤኤስዲ ሕክምና ምርመራ ያገኘ ከሆነ፣ እነርሱ የልጃቸዉን ጤና ኢንሹራንስ አቅራቢ በማግኘት ያላቸዉን ኢንሹራንስ ጥቅማጥቅሞች መገንዘብ አለባቸዉ። | **ጠንካራ አጀማመር** ከአምስቱ የእድገት ክፍሎች በአንዱ የ 25% መዘግየት ከታየ በኢንዲቪጂዋል ፋሚሊ ሰርቪስ ፕላን(አይኤፍኤስፒ) አማካኝነት አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ይሆናል። እነርሱ “የእድገት መዘግየቶችን ወይም እክሎችን” ለይተዉ የሚያዉቁ ይሆናል ነገር ግን የኤኤስዲ የትምህርት ምደባ ወይም ምርመራ **አያቀርብም**።<br><br>**ቀዳሚ ደረጃዎች**: እነዚህ ግምገማዎች በአይዲኢኤ-ተለይተዉ በሚታወቁ 14 እክሎች(ኦቲዝም ያካትታል) በአንዱ ልጁ መስፈርት ማሟላቱን ለይቶ ለማወቅ ጥቅም ላይ ይዉላሉ እና ኢንዲቪጂዋል ኤዱኬሽን ፕላን(አይኢፒ) መዘጋጀቱን የሚያሳዉቅ ይሆናል። ግምገማ የኤኤስዲ ትምህርታዊ ምደባ ዉጤት ሊፈጥር ይችላል ነገር ግን ቀዳሚ ደረጃዎች የኤኤስዲ የሕክምና ምርመራ የሚቀርብ አይሆንም። ቀዳሚ ደረጃዎች የአይኢፒ አገልግሎቶችን የሚያዘጋጅ እና የሚመክር ይሆናል። አይኢፒ አገልግሎቶች በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት(ዲሲፒኤስ ወይም ዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት) ቅንብሮች ስር ይተገበራል። | ወላጆች የግምገማቸዉን ዉጤቶች ለልጃቸዉ ጤና እና ትምርት አቅራቢዎች ማጋራት አለባቸዉ።<br><br>ወላጆች ቀጣይ ከሆኑ ድጋፎች እና አቅርቦቶች ጋር መገናኘት አለባቸዉ:<br>• **ዲሲ ኦቲዝም ፓረንትስ (ዲሲኤፒ)** 501(ሐ)3፣ ወላጆች-በፍቃደኝነት የሚመሩት ለትርፍ-ያልተቋቋመ ድርጅት ነዉ። ዲሲኤፒ ወርሃዊ ዜና መጽሄት፣ የድጋፍ ቡድን ስልክ ጥሪዎች፣ እና ስልጠናዎችን ለቤተሰቦች ያቀርባል።<br>• የወላጆች ስልጠና እና መረጃ (ፒቲአይ) ማእከል፣ **ለፍትህ እና ትምህርት ተሟጋቾች**። የፒቲአይ ግብ ከዉልደት እስከ-22 ዓመት እድሜ የሆናቸዉ እክሎች ያሉባቸዉ ልጆች ቤተሰቦችን የልጃቸዉን ትምህርት ከፍ ለማድረግ ነጻ መረጃ በመስጠት መደገፍ ነዉ። |

DC AC

DC AUTISM COLLABORATIVE

## ዲሲ ኦቲዝም ኮላቦሬቲቭ

**የእድገት ቁጥጥር፣ ማጣራት፣ እና የግምገማ ንዑስቡድን:**

ኢሚሊ አሮን፣ አዜብ አደሬ፣ ሻንተር አሌክሳንደር፣ ጄን አንደርሰን፣ ትሪና አንደርሰን፣ ራሄል ብሬዲይ፣ ቶሪ ብሮናዉህ፣ አይቪ ጊዘርማን-ኪስ፣ ሊአንድራ ጎዶይ፣ ዮላንዳ ግሬቭስ፣ ሳማንታ ሀምበርገር፣ አማንዳ ሃስቲንግስ፣ ዲያና ጃኮብስቲን፣ ሻሊን ኩሁራና፣ ስታሲ ላሞር፣ ቤኪ ሌን፣ ሜሊሳ ሎንግ፣ ማይክል ሚንትስ፣ የታ ማይሪክ፣ አላን ፊሊፕስ፣ ጆርዴን ሪደር፣ ካርላ ሪይድ-ዊት፣ ሊዝ ሪሃኒ፣ ካቲይ ሼይነር፣ አዉድሬይ ትሁርን፣ ያግናሽ ቫድጋማ፣ ሜሪ ዎዝኒያክ